# Asylum Advice

## ድህረ ውሳኔ - አዎንታዊ

# ድህረ ውሳኔ - አዎንታዊ

በዚህ ክፍል የጥገኝነት ጥያቄዎ መታየቱን ተከትሎ “በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየት ”ፍቃድ ከተሰጠዎት ምን ሊያጋጥም እንደሚችል በዝርዝር ቀርቧል። የሚከተለው መረጃ በመቀጠል ምን ሊያጋጥም እንደሚችል ያብራራል።

## 4A.1 የጉዳዬ ዓይነት ማለት ምንድን ነው?

Home Office ሊሰጠኝ የሚችለው ሶስት ዓይነት ደረጃዎች አሉኝ፡-

**1. የስደተኛ ሁኔታ**

እንደ ስደተኛ እውቅና ተሰጠህ ማለት Home Office በስደተኞች ስምምነት ስር የስደተኛነትህን ትርጓሜ ማሟላትህን እንደወሰነ እና ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱ ወይም ከዛ በላይ በሆኑት እንግልት እንደሚደርስብህ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ፍርሃት እንዳለብህ ተቀባይነት አግኝቷል ማለት ነው። ዘርህ ፣ ሐይማኖትህ ፣ ብሔርህ ፣ የአንድ ልዩ ማህበራዊ ቡድን አባል መሆንህ ወይም የፖለቲካ አስተያየት ማራመድህ።

Home Office ለ5 ዓመት ቆይታ ጊዜያት (ይህ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የመቆየት መብት ነው) ፍቃድ ይሰጥሃል። የአንተ የባዮ ሜትሪክ እና የHome Office ወረቀቶች በስደተኛነት እውቅና እንደተሰጠህ ያረጋግጣሉ።

የዘመኑ የስደተኝነት ፖሊሲ እንደሚያረጋግጠው በስደተኝነት ሁኔታ እና በበጎ አድራጎት ከለላ ከ 5 ዓመታት ቆይታ በኋላ “ላልተወሰነ የቆይታ ፍቃድ ጊዜ” (በጊዜ መወሰኛ ላይ ያልተመሰረተ ፈቃድ፣ ይህ በአብዛኛው “ሰፈራ” ተብሎ የሚጠቀሰው ነው) ለማመልከት ትችላለህ።

ቢሆንም ግን አንተ ወይም ማናቸውም ጥገኞችህ በወንጀል ጥፋት ከተከሰሳችሁ ፣ ማመልከቻችሁ ውድቅ መደረግን ሊያስከትልባችሁ ይችላል።

**2. የሰብዓዊነት ጥበቃ**

ይህም Home Office አንተ የስደተኝነት ሁኔታን መስፈርት እንደማታሟላ ወስኗል ማለት ነው። ግን ወደ ትውልድ አገርህ ከተመለስክ ከባድ አደጋ በእውነተኛነት ሊጋረጥብህ እንደሚችል የሚያሳዩትን ምክንያቶች ተቀብሏል ማለት ነው።

ይህም በሚመከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል

- የሞት ቅጣት/አፈፃፀም
- ሕገ ወጥ ግድያ
- ግርፊያ ወይም ድብደባ
- ኢሰብአዊ ድርጊት እና አዋራጅ አያያዝ
- ቅጣት ወይም ከባድ እና ግለሰባዊ የሕይወት ስጋት በአለም አቀፍ ወይም በአገር ውስጥ

በሚካሄድ በመሳሪያ የታገዘ ግጭት ሁኔታዎች ማንንም ያልለየ ብጥብጥ መካሄዱ።

የበጎ አድራጎት ከለላ ከተሰጠህ ፣ “የመቆየት ፍቃድ” (የቆይታ መብት) በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለ5 ዓመታት ይሰጥሃል። የሰነድ ማስረጃህ በበጎ አድራጎት ምክንያቶች ፍቃዱ እንደተሰጠህ ያረጋግጣል።

የዘመኑ የስደተኛ ፓሊሲ እንደሚገልፀው ከ5 ዓመታት የበጎ አድራጎት ጥበቃ ቆይታ በኋላ “ላልተወሰነ የቆይታ ፈቃድ” ለማመልከት ትችላለህ።

**3. የመቆየት ፍቃድን በስልጣን ስለመወሰን**

Home Office የሰብአዊ ጥበቃ ወይም የስደተኛ ሁኔታን መስፈርቶች እንደምታሟላ ካልተቀበለህ ፣ ግን በእግሊዝ አገር ውስጥ በጊዜያዊነት ለመቆየት የሚያስችሉህን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ከተቀበለ ፣ “በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየት በመወሰን ሥልጣን የሚሰጥ ፍቃድ” (የመቆየት መብት) ይኖርሃል።

በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየት በመወሰን ሥልጣን የሚሰጥ ፍቃድ ብዙውን ግዜ ቢበዛ በአንድ ጊዜ ለሁለት ዓመት ተኩል (ለ30 ወራት) የሚሰጥ ይሆናል። ፍቃድህን ለማራዘም ልታመልክት ትችላለህ፣ እና ከ10 ዓመት በኋላ “ላልተወሰነ የቆይታ ፈቃድ” ለማመልከት ትችላለህ።

## 4A.2 የስደተኛ ሁኔታ ካልተረጋገጠልኝ ይግባኝ ለማቅረብ እችላለሁን?

የሰብአዊ ጥበቃ ወይም በመወሰን ሥልጣን ላይ የተመሰረተ ፍቃድ ከ12 ወራት በላይ ከተሰጠህ፣ ግን ለስደተኛ ሁኔታ ጠንካራ መሰረቶች እንደነበሩህ ካመንክ በመቀጠል የ Home Office ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት ትችላህ። ይህም የተሻሻለ ይግባኝ ተብሎ ይጠራል፤ ከሕግ አማካሪህ ጋር መወያየት ያስፈልግሃል። ስኬታማ ከሆነክ የስደተኛ መብት ይሰጥሃል።

## 4A.3 ፍቃዴ ሊያበቃ ሲል ምን ይከሰታል?

የቆይታ ፍቃድህ ጊዜያት ሊያበቃ አካባቢ ለ Home Office ተጨማሪ ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልግሃል። ፍቃድህ እያለቀ ከመሄዱ 28 ቀናት ቀድመህ ብቻ ማመልከት ትችላለህ።

ማመልከቻህን የዘመኑ ፍቃድህ ከማብቃቱ በፊት መቀበሉ በጣም ጠቃሚ ነው። Home Office የዘመኑ ፍቃድህ ከማብቃቱ በፊት በማመልከቻህ ላይ ውሳኔ ካልሰጠህ፣ በመቀጠል እንደበፊቱ ተመሳሳይ መብቶችን ይዘህ ትቀጥላለህ። ማመልከቻህ በHome Office የፍቃድ ቆይታህ ካበቃ በኋላ ተቀባይነት ካገኘ በመቀጠል ፣ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ በጣም በከፍተኛ ደረጃ ሕገ ወጥ የመሆን እድል ይኖርሃል። ይህም ማለት የመስራት ፣ ጥቅማ ጥቅም እና ሁሉንም ከፍቃድህ ጋር ተዛማጅ የሆኑ መብቶችን በሙሉ የመጠየቅ መብትህን ታጣለህ ማለት ነው።

ይህ ከሆነ ደግሞ ፣ በአስቸኳይ የሕግ አማካሪ ያስፈልግሃል። ስለእንደዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ከHome Office የስደተኛ ድህረ ገጽ መረጃ ሊገኝ ከቻለ።

በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየት “በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመቆየት በመወሰን ሥልጣን የሚሰጥ ፍቃድ” ከተሰጠህ ፣ “ለተጨማሪ የቆይታ ፍቃድ” ለማመልከት

ትችላለህ። ተጨማሪ ፍቃድ አንድ ጊዜ በፓሊሲው ስር ብቁ መሆንህን እንደቀጠልክ የሚሰጥህ ይሆናል። ይህንንም ማድረግ የሚያስፈልግህ ለ10 ዓመታት በድምሩ ፍቃድ እስክታገኝ ድረስ ይሆናል። ለተጨማሪ የቆይታ ፍቃድ ለማመልከት አስፈላጊውን መረጃ ከ Home Office ድህረ ገጽ ለማግኘት ትችላለህ። www.gov.uk/browse/visas-immigration ከዚህ ነጥብ በኋላ “ላልተወሰነ የቆይታ ፈቃድ” ለማመልከት ትችላለህ። ማመልከቻህ ስኬታማ ከሆነ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ በመቆየት መብትህ ላይ ምንም ዓይነት የጊዜ መወሰኛ አይኖርም።

ጠቃሚ ማስታወሻ፡- በጊዜ ሂደት በስደተኛ ፓሊሲዎች ላይ ለውጥ የሚያመጡ ማናቸውንም ለውጦች በየጊዜው ማሻሻል ጠቃሚ ነው። ይህንንም የHome Office ድህረ ገጽን በመከለስ ልታካሂድ ትችላለህ። www.gov.uk/browse/visas-immigration

## 4A.4 ምን ዓይነት የወረቀት ሥራ ይሰጠኛል?

የባዮ ሜትሪክ ካርድ

የባዮ ሜትሪክ መኖሪያ ፈቃድ (የባዮ ሜትሪክ ካርድ) ትቀበላለህ። ይህ ሰነድ ካንተ ARC ጋር ተመሳሳይ ነው። የባዮ ሜትሪክ ካርድ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የመቆየት የመስራት እና የመማር መብትህን የሚያረጋግጥ ነው። የባዮ ሜትሪክ ካርድን እንደ መታወቂያ ካርድ ልትገለገልበት ትችላህ። በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የባንክ ሂሳብ ለማግኘት ስታመለክት ማሳያት ያስፈልግሃል። ይህንን ካርድ ሁልጊዜ መያዝ አያስፈልግህም ግን በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ያለህን መብት እና ጥቅም ለማረጋገጥ ማሳየት ያስፈልግሃል።

የባዮ ሜትሪክ ካርድህ ለአንተ ወይም ለሕግ አማካሪህ አስተማማኝ በሆነ መልዕክት የሚለጠፍ ይሆናል። ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባልህ ካርድ ትቀበላለህ።

የባዮ ሜትሪክ ካርድህ ስምህን ፤ ፆታ ፤ የትውልድ ቀን እና ቦታ ፤ ፎቶግራፍ የስደተኛ ሁኔታ ፤ ፍቃድህ መቼ እንደሚያበቃ ፤ የመብት ዝርዝሮች እና ፊርማህን ያሳያል። በካርዱ ላይ ያለው የባዮሜትሪክ ቺፕ ያንተን የጣት አሻራዎች እና የፊት አምሳያ የያዘ ነው።

ጠቃሚ ማስታወሻ፡- ሁሉም ባከርዱ ላይ ያሉ ዝርዝሮች ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብህ። ማናቸውን ስህተቶች ለHome Office ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለብህ። ዶኩመንቱ ከተላከላችሁ በኃላ ስህተር ካለው በ10 ቀን ውስጥ ስህተቱን ልታሳውቁን ይገባል። ይህ ካላደረጋችሁ ግን እንደገና እንደ አዲስ ማመልከቻ ማቅረብ እና ለአዲሱ ካርድ መላኪያ ትከፍላላችሁ ማለት ነው። መኢመይል አድርጋችሁ ልታሳውቁን ትችላላችሁ፡ አድራሻው; BRPError@homeoffice.gsi.gov.uk ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነገሮች ማስገባት አለባችሁ።

- የፓስፖርት ቁጥር
- የባዮመትሪክ መኖሪያ ፍቃድ ቁጥር
- የጉዳያችሁ መዝገብ ቁጥር
- ተሌፎን ቁትራችሁ በቀላሉ መገናኘት እንድንችል
- ስህተት ምን እንደሆነ የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ

**የባዮሜትሪክ ካርዴ ቢጠፋብኝስ ?**
**የባዮሜትሪክ ካርድህ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ ፣ ይህንን በታቻለ ፍጥነት ለ**Home Office **ሪፖርት ማድረግ አለብህ። የ** Home Office **የባዮሜትሪክ ካርድህን መሰረዝ ያስፈልገዋል።**
**ካርድህን በሕግ እንድትሰርዘው እና ለ**Home Office **በሚከተለው የኢሜል አድራሻ እንድታስታውቅ ትጠየቃለህ፡-** BRPLost@homeoffice.gsi.gov.uk.

**በኢሜልህ ውስጥ እንደሚከተለው መግለጽ አለብህ፡-**

- **ሙሉ ስምህን፣**
- **የትውልድ ቀን፣**
- **ዜግነት፣**
- **ፓስፖርት ቁጥር፣**
- **የባዮ ሜትሪክ ካርድ ማጣቀሻ ቁጥር፣**
- **የጉዳይ ማጣቀሻ ቁጥር፣**
- **የግንኙነት ዝርዝሮች፣ እና**
- **ፍቃዱ መቼ የት እና እንዴት እንደጠፋ ወይም እንደተሰረቀ።**

**መጥፋቱን ወይም መሰረቁን ለፓሊስ የግድ ማመልከት እና የፓሊስ ሪፖርት እና የወንጀል ማጣቀሻ ቁጥር በተቻለ ፍጥነት ማግኘት አለብህ። ይህ መታወቂያ ካርድ ተሰርቆ ሆነ ገበኑ ለፖሊስ ማሳወቅ አለባችሁ። መታወቂያ ካርዱ ጠብቶባችሁ ከሆነ ግን ሁኔታው በሚቀጥለው አድራሻ ተጠቅማችሁ ማሳወቅ አለባችሁ።** https://www.reportmyloss.com **አዲሱ ካርድ እንዲላክላችሁ የተለያዩ ቦታዎች ያምትከፍሉት ገንዘብ መጠን** £3.95 **ነው። ይህ ለማድረግ የባንክ ሒሳብ ደቢት/ክረዲት ካርድ ያስፈልጋቸውል።**

**የባዮ ሜትሪክ ካርድ እንዲተካልህ ማመልከት ያስፈልግሃል። ይህንን አስመልክቶ መረጃው ከ** Home Office **ድረገጽ ሊገኝ ይችላል።** www.gov.uk/biometric-residence-permits

**የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር** (NINO)
**በዋና ቃለ መጠይቅ ክፍልህ ፣ ስለ የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር ተጠይቀህ ነበር። የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር** (NINO) **ለአንተ ልዩ የሆነ የማጣቀሻ ቁጥር ነው። ይህም ለዩናይትድ ኪንግደም** (UK) **ለብሔራዊ መድን ምዝገባ እና የማህበራዊ ዋስትና ሥርዓት በጥቅም ላይ ይውላል። ይህንን ሕይወትህን በሙሉ መጠበቅ ያስፈልግሃል። የብሔራዊ መድን መዋጮዎች እና የምትከፍለው ግብር በስምህ አንፃር በአግባቡ መመዝገቡን ያረጋግጣል። ከሥራ እና ጡረታ ሚኒስቴር እንዲሁም ከገቢዎች እና ጉሙሩክ ባለስልጣን ጋር ግንኙነት ስታደርግ በማጣቀሻ ቁጥርነት ያገለግላል።**

**የብሔራዊ መድን ቁጥሮች በተለምዶ ከ**16 **ዓመት ዕድሜ በላይ ለሆናቸው ሰዎች ይሰጣሉ።**

**አዋቂ ጥገኞች በጥገኝነት ማመልከቻ ጊዜያት የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር** (NINO) **ይጠየቃሉ። ስለዚህም ወዲያውኑ የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር** (NINO) **አትቀበልም። የሥራ እና ጡረታ ሚኒስቴርን ለመገናኘት እና ለጥገኞችህ የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር** (NINO) **እንዲያዘጋጁላቸው**

ማድረግ አለብህ።

ሥራ ለመጀመር ወይም የራስህ ተቀጣሪ ለመሆን ለብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር (NINO) ማመልከት ያስፈልግሃል ፣

በመቀጠል የሥራ ማዕከል + በ 0845 600 0643 መገናኘት ያስፈልግሃል

ለጥቅማጥቅም የምታመለክት ከሆነ የሥራ እና ጡረታ ሚኒስቴር (ዲደብልዩፒ የሥራ ማዕከል) የብሔራዊ መድን ቅጽን በሥራ ማዕከል ቃለ መጠይቅ ጊዜያት ይሞላል። ይህም “ዲሲ 1 1 ቢ ቅጽ” ‘DCI 1B form ተብሎ ይጠራል። ይህም ለአንተ የብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር (NINO) እንዲሰጥህ ይጠይቃል።

ለብሔራዊ ኢንሹራንስ ቁጥር (NINO) ቃለ መጠይቅ ከተጠራህ ፣ ማንነትህን እና በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለመስራት በቂ መሆንህን ማረጋገጥ ያስፈልግሃል። የባዮ ሜትሪክ ካርድ ይህንን ለማረጋገጥ ሊያገለግል ይችላል። እንዲሁም ሌሎች የመታወቂያ ሰነዶችን ከአንተ ጋር እንድትወስድ ልትጠየቅ ትችላለህ። ከአንተ ጋር ምን ዓይነት መረጃዎችን መውሰድ እንደሚያስፈልግህ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጥሃል።

## 4A.5 የመልሶ መቋቋሚያ ብድር ዝርዝር መረጃ

ለሰብአዊ ጥበቃ ወይም የስደተኛ ሁኔታ ማረጋገጫ ካገኘ የመጠናከሪያ ብድር ለማግኘት ትችላለህ። ብድር በመልሶ መጠናከር የመጀመሪያ ደረጃዎች አንተን ለማገዝ የብድር ዝግጅት የሚካሄድበት ነው። ብድር የመጠናከሪያ ሂደትን እንደ ያሉትን ክፍሎች እና ተግባራት ለማፋጠን በጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፦

- ሞያዊ ስልጠናው በ Job Centre Plus አማካኝነት የማይቀርብ ከሆነ። ይህም ከሥራ ማዕከል አማካሪ ጋር ውይይት ሊደረግበት ይገባል።
- የመኖሪያ ቤት ተቀማጭ፤
- ለቤት የሚያገለግሉ አስፈላጊ ዕቃዎችን መግዛት፤ ወይም
- ለንግድ የሚሆኑ መስሪያዎችን መግዛት።

የባንክ ሂሳብ ከሌለህ ፣ ቢበዛ እስከ 450 ፓውንድ ድረስ ለማመልከት ትችላለህ። ስለዚህም ከዚህ ለበለጠ መጠን የምታመለክት ከሆነ የባንክ ሂሳብ መክፈትህ ጠቃሚ ነው። የብድር መልሶ ክፍያዎች በሥራ እና ጡረታ ሚኒስቴር (DWP) በመደበኛ መልኩ በሚከፈሉ ክፍያዎች መሰብሰብ ያስፈልጋቸዋል። ይህም በቀጥታ ከጥቅማጥቅሞችህ ወይም ከባንክ ሂሳብ በሚደረግ ቀጥተኛ ወጪ አማካኝነት ይሆናል። በአብዛኛዎቹ የብድር መልሶ ክፍያ ሁኔታዎች ውስጥ ገንዘቡ ለተበዳሪው በተለቀቀ በ6 ሳምንታት ውስጥ ይጀምራሉ። ብድሩ ከመከፈሉ በፊት የብድር ስምምነት መፈረም ያስፈልጋል። ያለ ብሔራዊ የኢንሹራንስ ቁጥር የመልሶ መቋቋሚያ ብድር እንዲሰጥህ ማመልከት አትችልም። ብመቁ ሳይኖህ ማመልከት ማመልከቻህ እንዳልተሟላ እና ውድቅ እንደተደገረ ተቆጥሮ ይመለስልሃል። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በሚቀጥለው የኢንተርኔት አድራሳ ገብተው ይመለከቱ። www.gov.uk/refugee-integration-loan/overview

## 4A.6 NASS 35

ከ Home Office ድጋፍ የምታገኝ ከሆነ NASS 35 ትቀበላለህ። ይህ በኤ4 የተለበደ ሰነድ የአንተን ፎቶ እና የድጋፍ ዝርዝሮችን ያካተተ ነው። ይህም ከ Home Office የድጋፍ ቡድን ለአንተ የሚላክ ይሆናል። የተቀበልከውን ድጋፍ እና ድጋፉ መቼ እንደሚያቆም ያረጋግጣል። ሁሉም ከ Home Office የምታገኛቸው ድጋፍ አንተ ወይም የሕግ አማካሪህ የውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሳቸው ቀን ጀምሮ በ28 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃሉ። ስለዚህ NASS 35 የሚመለከት ተጨማሪ እርዳታ ካስፈለጋችሁ ወደ Asylum Help (አሳይላም ሄልፕ) በሚቀጥለው ስልክ ቁጥር ደውለው ይገናኙን። 0808 8000 622

## 4A.7 ራሴን እና ቤተሰቤን እንዴት ለመደገፍ እችላለሁ?

3 Home Office የሁኔታህን ማስታወቂያ ከተቀበልክ ከ28 ቀናት በኋላ አንተን የመደገፍ ግዴታ የለበትም። ከ Home Office እና ከመኖሪያ አቅራቢው (በ Home Office የምተደገፍ) ከሆነ ከሁለቱም ደብዳቤ ትቀበላለህ ይህም ድጋፉ መቼ እንደሚያቆም እና መኖሪያውን መቼ ለቀህ መውጣት እንዳለብህ ያረጋግጣል መኖሪያውን በተባለው ቀን ሁሉንም ንብረቶችህን በመያዝ አገሪቱን ለቀህ መውጣት አለብህ።

## 4A.8 መኖሪያ ቤት፡- እንግሊዝ እና ዌልስ

የመኖሪያ ቅድሚያ አስፈላጊነት (የችግር ግዜ/ጊዜያዊ መኖሪያ) ቤት አልባ ከሆንክ የአካባቢው ምክር ቤቶችን የቤቶች መስሪያ ቤት ድጋፍ እንዲያቀርቡልህ መጠየቅ ትችላለህ። ነዋሪ በሆንክበት አካባቢ የሚገኘው ምክር ቤት ለአንተ ምክር እና ድጋፍ እንዲሰጥ በሕግ ይጠየቃል። በግል ሁኔታዎችህ ላይ ተመስርቶ ፣ ለአንተ መኖሪያ ማቅረብ አለባቸው።

ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ብለህ ካሰብክ ፣ ይህ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፤ በቤተሰብ ውስጥ ካሉት ሕፃናት ልጆች ውስጥ በከባድ ህመም - በአእምሮ ወይም አካላዊ ሕመም የሚሰቃይ ፣ በቤት ውስጥ ጥቃት የመጋለጥ አደጋ ያለው፣ የቤቶች ቢሮ ለአንተ መኖሪያ ማቅረብ ያስፈልገዋል። የቤት አልባነት ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልግሃል። የአካባቢው ምክር ቤት ለአንተ መኖሪያ የማቅረብ ግዴታ እንደላባቸው ለመወሰን ይህንን ይመዝናሉ። አንተ ቤት አልባ መሆንህን ወይም ያለመሆንህን ፣ ቅድሚያ ሊሰጥህ እንደሚገባ ፣ ራስህን ቤት አልባ ያደረግከው በምርጫህ እንደሆነ እና ወይም የአካባቢ ግንኙነት እንዳለህ ይመዝናሉ።

ምክር ቤቱ አንተን እንደ “ቅድሚያ ፍላጎት” ከመዘነህ የድንገተኛ ወይም የጊዜያዊ ቤት አቅርቦት ይቀርብልሃል። የድንገተኛ መኖሪያ አልጋ እና ቁርስ ወይም የሆስቴል መኖሪያ ሊሆን ይችላል። ሕጉ እንደሚለን ምክር ቤቶች ቤተሰቦቹን እና ነፍሰጡር ሴቶችን በአልጋ እና ቁርስ አቅርቦቶች ከ6 ሳምንታት በላይ መጠበቅ የለባቸውም። ከሚከተሉት ምክር መሻት ትችላለህ

መጠለያ - ሁሉንም የቤት አቅርቦት መብቶች አስመልክቶ ገለልተኛ ምክር ሊሰጡህ እና በስልክ ቁጥር 0800 800 4444 ልታገኛቸው ትችላለህ።

በአካባቢህ ውስጥ ገለልተኛ የቤቶች አማካሪ ማዕከል ልታገኝም ትችላለህ።

ምክር ቤቱ ቤት አልባ መሆንህን ከተቀበለው እና አንተን የማኖር ግዴታ እንደላባቸው ከተስማሙበት። ሊያቀርቡልህ ይችላሉ፡-

1) የምክር ቤቱ ቤት አቅርቦት
2) የቤቶች ማህበር ቤት አቅርቦት
3) አስተማማኝ ለረዥም ጊዜ በግል የተከራየ መኖሪያ ቤት።

ምክር ቤቱ ከዚህ በላይ ካሉት የመኖሪያ ዓይነቶች ማናቸውን ሊያቀርብልህ ይችላል። አንድ ጊዜ የምቹነት ማቅረቢያ ከተደረገ ግዴታቸው ያበቃል።

መኖሪያው አመቺ አይደለም ብለህ ካመንክ ጥያቄውን ከመቃወምህ በፊት ገለልተኛ ከሆነ አካል በጉዳዩ ላይ ምክር ማግኘትህ ጠቃሚ ነው። የመኖሪያ አቅርቦትን ከተቃወምክ እና ለአንተ ፍላጎቶች አመቺ ሆኖ ካልተገኘ፣ በመቀጠል ምክር ቤቱ ለአንተ ያለበትን ግዴታ የማቆም መብት አለው። ራስህን ሆን ብለህ ቤት አልባ እንዳደረግክ በመቁጠር ማንኛውንም የድንገተኛ ቤት አቅርቦትን ለማቋረጥ ይችላል።

ሸልተር የተባለው ድርጅት ሁሉንም የቤት መብቶች አስመልክቶ ገለልተኛ ምክር ሊሰጡህ ስለሚችሉ በስልክ ቁጥር 0800 800 4444 አግኛቸው።

በአከባቢህ የግል መኖሪያ ቤት አማካሪ ማዕከል ለማግኘት ትችላለህ። .

የግል መኖሪያ ቤት
ቅድሚያ ሊሰጥህ እንደማይገባ ከተቆጠርክ ፣ የግል የተከራየ መኖሪያ መፈለግ ያስፈልግሃል።

ቅድሚያ ሊሰጥህ እንደሚገባ እና ምክር ቤቱ ያለአግባብ እንደወሰነብህ ካመንክ ይግባኝ ለማለት ትችላለህ። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ገለልተኛ የሕግ ምክር ለመሻት ያስፈልግሃል።

አስተማማኝ መኖሪያ ማግኘት ካለብህ ፣ አብዛኛዎቹ ቤት አከራዮች ተቀማጭ እና የሙሉ ወራት ኪራይ ይጠይቃሉ። የአከባቢያዊ የቤቶች ኤጀንሲ በዚህ አካባቢ ውስጥ ማንኛውም ድጋፍ ወይም እርዳታ ሊቀርብልህ እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ ይወስናል። ለምሳሌ የአካባቢያዊ ቦንድ ወይም የኪራይ ተቀማጭ ዝግጅት ለኖርህ ይችላል። እንዲሁም በዚህ ረገድ ድጋፍ ለማግኘት የመጠናከሪያ ብድር ለማመልከትም ትችላለህ።

የጎዳና ተዳዳሪነት
ራስህን በጎዳና ላይ ነዋሪ ቤት አልባ ሆነህ ካገኘኸው ፣ አንተን ምናልባት ለመርዳት በአካበቢህ የሚሰሩ ድርጅቶች ይኖራሉ። በአጠገባችሁ የሚገኝ የመንግስ ቤት ጽሕፈት (ማዛጋጃ ቤት ስለዚህ ሁኔታ ሊረዳችሁ ይችላል፡ በአከባቢያችሁ የሚገኝ ድርጅቶች ዝርዝር እንዲሰጣችሁ እና ምናልባትም ሊረዳችሁ ይችላል። ይህ ደግሞ ምናልባት በአደጋ ውስጥ እንዳትገቡ ደህና የሆነ መተኛ ቦታ ሄዳችሁ የምትተኙበት ቦታ ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ሙቅ ምግብ የሚሰጥበት ቦታ ሊሆን ይችላል።

SHELTER ጋር በመገናኘት፣ ስለሁሉም የቤት አቅርቦት መብቶች ገለልተኛ ምክር ሊሰጥህ እና

በስልክ ቁጥር 0800 800 4444 ማግኘት ይቻላል።

የሚከተሉትንም ለማግኘት ትችላለህ፡-

የቀን አገልግሎቶች - በምግብ በአልባሳት እና በመታጠቢያ ቤት ሊረዱህ ይችላሉ። ገለልተኛ ምክርንም ሊያቀርቡልህ ይችላሉ።

የአስቸኳይ ጊዜ ሆስቴሎች እና የምሽት መጠለያዎች - ለጥቂት ጊዜያት ራስህም በጎዳና ላይ ካገኘኸው ለተወሰኑ ምሽቶች መኖሪያ ለማግኘት ትችላለህ።

STREETLINK ጋር በስልክ ቁጥር 0300 500 0914 በመገናኘት ምክር ሊያቀርቡልህ ይችላሉ።

## 4A.9 መኖሪያ፡ ስኮትላንድ

ልትቆይበት የምትችልበት ምንም ቦታ ከሌለህ፣ የአካባቢውን ምክር ቤት የቤቶች መስሪያ ቤት ለመጠየቅ ትችላለህ። በምትኖርበት አካባቢ የሚገኘው ምክር ቤት ለአንተ መክር እና ድጋፈ እንዲሰጥ በሕግ ይጠየቃል። የቤት አለባነት ማመልከቻ ካቀረብክ የቤቶች መስሪያ ቤት ብቁነትህን በመመዘን ላይ እያለ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ይቀርብልሃል። ምክር ቤቱ በዚህ አካባቢ ውስጥ ምንም ዓይነት መኖሪያ ከሌለው፣ ከዚህ አካባቢ ውጪ መኖሪያ ሊያቀርቡልህ ይገባል።

አንተን የመድገፍ ግዴታ እንዳለባቸው ከወሰኑ ፣ በመቀጠል ቋሚ መኖሪያ ያቀርቡልሃል። በጊዜያዊ መኖሪያህ ውስጥ ቋሚ መኖሪያ እስኪቀርብልህ ድረስ ለመቆየት ትችላለህ።

ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ድጋፍ የማቅረብ ግዴታ ከሌለባቸው፣ በመቀጠል በአስቸኳይ ጊዜ መኖሪያ ውስጥ ቋሚ መኖሪያ እስክታገኝ ድረስ ለመቆየት ትችላለህ። ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ መኖሪያ ቤት ካላቀረበልህ ፣ በመቀጠል የቤቶች አማካሪ ማስሪያ ቤትን ድጋፍ ለመገናኘት ትችላለህ።

በቤት አልባነት ሁኔታ ውስጥ የምትገኝ ከሆነ ፣ የአስቸኳይ ጊዜ መኖሪያ ቤት አማራጮች፡-

- ሆስቴሎች ፣ የምሽት መጠለያዎች እና የክረምት መጠለያዎች
- የቤት ውስጥ ጥቃት እና የሴቶች ስደተኞች
- አልጋ እና የቁርስ ሆቴሎች።

የአካባቢ ምክር ቤት የበለጠ መረጃ ሊሰጥህ ይገባል። ከአካባቢው የቤቶች ኤጀንሲ ድጋፍ መጠየቅ አለብህ። በዋጋ ረገድ እንዲረዳህ ለቤቶች ጥቅማጥቅም ልታመለክት ትችላለህ። አንዳንድ የመኖሪያ አማራጮች በጣም ውድ እና ኪራይህን ለመክፈል የቤቶች ጥቅማጥቅም ከፍ እንዲል ማድረግ ሊያስፈልግህ ይችላል።

ጠቃሚ ማስታወሻ፡- የአካባቢው የቤቶች መስሪያ ቤት ወይም የቤት አቅርቦት አማካሪ ማዕከል በአካባቢ ውስጥ ማናቸውም የምሽት መጠለያዎች ወይም ሆስቴሎች ካሉ ማረጋገጥ ትችላለህ።

ለበለጠ መረጃ ፣ እባክህን ሼልተርን በስልክ ቁጥር 0800 800 4444 ተገናኝ። አግባብነት ስላላቸው አገልግሎቶች ገለልተኛ ምክር እና ምልክት ሊሰጡህ ይችላሉ።

## 4A.10 መኖሪያ ቤት፡- ሰሜን አየርላንድ

የሰሜን አየርላንድ የመኖሪያ አቅርቦት አስፈጻሚ ቤት አልባ ከሆንክ ድጋፍ እና ምክር የማቅረብ ሕጋዊ ግዴታ አለበት።

በግላዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ፣ ለአንተ መኖሪያውን ሊያቀርቡልክ ይችላሉ።

የቤት አልባነት ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልግሃል። NIHE ለአንተ መኖሪያ ቤት የማቅረብ ግዴታ እንደላባቸው ለመወሰን ይህንን ይመዝናሉ። አንተ ቤት አልባ መሆንህን ወይም ያለመሆንህን ፣ ቅድሚያ ሊሰጥህ እንደሚገባ ፣ ራስህን ቤት አልባ ያደረግከው በምርጫህ እንደሆነ እና ወይም የአካባቢ ግንኙነት እንዳለህ ይመዝናሉ። ጉዳይህን እስኪመረምሩ ድረስ ለአንተ ጊዜያዊ መኖሪያዎችን ያቀርቡልሃል።

ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ብለህ ካሰብክ ፣ ይህ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡- በቤተሰብ ውስጥ ካሉት ሕፃናት ልጆች ውስጥ በከባድ ህመም - በአእምሮ ወይም አካላዊ ሕመም የሚሰቃይ ፣ በቤት ውስጥ ጥቃት የመጋለጥ አደጋ ያለው፣ የቤቶች ቢሮ ለአንተ መኖሪያ ማቅረብ ያስፈልገዋል። ይህ ፍላጎታቸው ቢያንስ ለ2 ዓመት ሊቀርብ ይችላል። የግዴታ ቋሚ መኖሪያ ቤት ማቀረብ አይኖርባቸውም።

ለበለጠ መረጃ ኤንአይኤችኢን በስልክ ቁጥር  03448 920 920 ተገናኝ

## 4A.11 የቤት አቅርቦት ጥቅማጥቅም ፣ የአካባቢ መኖሪያ አበል እና የምክር ቤቱ ግብር ጥቅማጥም

ዝቅተኛ ገቢ ካለህ ወይም የማህበራዊ ደህንነት ጥቅማጥቅሞች በመጠየቅ ላይ የምተገኝ ከሆነ፣ የቤቶች አቅርቦት ጥቅማጥቅምን ወይም አካባቢያዊ ቤቶች አበልን በቤትህ ላይ ከፊል ወይም ሁሉንም ኪራይ ለመክፈል እንዲረዳህ ልታገኝ ትችላለህ። ለዚህ ዓላማ ለምክር ቤቱ ልታመለክት ትችላለህ። እንዲሁም የምክር ቤቱን ግብር አስመልክቶ ድጋፍ ለማግኘት ልታመለክት ትችላለህ። በአብዛኛው የቤቶች ጥቅማጥቅም/የቤቶች ድጋፍ አበል በተመሳሳይ ቅጽ {34}. {35} ላይ ነው።

## 4A.12 የማህበራዊ ደህንነት ጥቅማጥቅሞች

Universal Credit (ዩኒቨርሳል ክረዲት) የመንግስት እርዳታ

መንግስቱ ቀስ በቀስ ለሰዎች የሚሰጣቸው የመንግስት እርዳታ በአንድ እንዲሰጥ እየቀየረው ነው። ይህ አገልግሎት Universal Credit (ዩኒቨርሳል ክረዲት) የሚባል ሰዎች ስራ የሚያፈላልጉ ወይም ደግሞ ሰዎች ስራ እስከሚያገኙ ድረስ ወይም ገቢያቸው በጣም አነስተኛ ለሆኑ የሚረዳ ነው። የተለያዩ እርዳታዎች በአንድ ላይ የ Job Seekers Alowance ጆብ ሲከርስ አለዋንስል፣ Houseing Benefit ሀውዚን በነፊት በአንድ ላይ አተቃልሎ የሚሰጥ እርዳታ ነው። Universal Credit (ዩኒቨርሳል ክረዲት) የሚባል የእርዳታ አሰጣት መንገድ ቀስ በቀስ ነው የሚዘረጋው

ያለው። ስለዚሁ ሁኔታ የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጋችሁ ስለዚሁ www.gov.uk/universal-credit ጥያቄ ካላችሁ Universal Credit (ዩኒቨርሳል ክረዲት) ጋር ትገናኛላችሁ ስልክ ቁጥራችን 0345 600 0723 (ስልክ መደወያ የሚከፈል ገንዘብ አለ)። ይህ Universal Credit (ዩኒቨርሳል ክረዲት) እርዳታ መጠየቅ ካልቻሉ በታች የተዘረዘሩት የመንግስት እርዳታ ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ።

የስራ ፈላጊዎች አበል (Job Seekers Allowance (JSA)
ይህ በአሁኑ ጊዜ ሥራ በመፈለግ ላይ ለሚገኙ ወይም በየሳምንቱ አማካይ ሥራ ሲቀነስ ከ16 ሰዓታት በታች ለሚሰሩ ግለሰቦች የሚቀርብ ጥቅማ ጥቅም ነው።

የሥራ ፈቀላጊዎች ስምምነት ወይም አዲሱን የይገባኛል መሰጠት ቅጽ መሙላት ያስፈልግሃል። ሥራ ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለብህ ያስቀምጣል። በድጋፍህ ምላሽ ሥራ ለማግኘት ማድረግ ያለብህን በሙሉ አስመልክቶ ኃላፊነትህን ይገልፃል።

የሥራ ፈላጊ አበል በመቀበል ላይ እያለህ ለሁሉም የሥራ ፍለጋ እርምጃዎችህ በመዝገብ መጠበቅ አለብህ። ይህንን መሰጠትህን ካላሟላህ ፣ የሥራ ማዕከል ጥቅማጥቅሞችህን ሊያግድ ወይም ሊያቆማቸው ይችላል።

የሥራ ማዕከል የስልጠና ኮርሶችን ለማግኘት ትችላለህ። ይህም የሚያካትታቸው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎችን (ESOL) ይሆናል። ይህንንም ከሥራ ማዕከል ጋር መወያየት ያስፈልግሃል።

የገቢ ድጋፍ
የገቢ ድጋፍ ለመኖሪያ የሚሆናቸው በቂ ገንዘብ ለሌላቸው የተወሰኑ ሰዎች ቡድኖች የሚከፈል ጥቅማጥቅም ነው። ይህም በዘዴ ላይ የተፈተነ ማለትም ያለህ ማንኛውም ገንዘብ ምን ያህል የገቢ ድጋፍ ማግኘት እንዳለብህ ለመወሰን ዓላማ ያገለግላል።

እንግሊዝ ፣ ስኮትላንድ እና ዌልስ
ለገቢ ድጋፍ ዓላማ ብቁ ለመሆን ከሚከተሉት ሁሉንም መሆን አለብህ፡-

- ከ16 ዓመት እና በጡረታ ገቢ ዕድሜ መካከል
- ነፍሰጡር ወይም ተንከባካቢ፣ ወይም ከ5 ዓመት በታች የሆነ ልጅ የሚንከባከብ ብቸኛ ወላጅ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች በመታተመምህ ወይም የአካል ጉዳተኛ በመሆንህ የተነሳ ለመስራት የማትችል
- ምንም ዓይነት ገቢ የሌለህ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ያለህ
- በሳምንት ከ16 ሰዓታት በታች ምትሰራ (እና የትዳር ጓደኛህ ከ24 ሰዓታት በላይ በሳምንት የማትሰራ)

ሰሜን አየርላንድ
በሰሜን አየርላንድ ውስጥ ለገቢ ድጋፍ ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን በሙሉ ማሟላት አለብህ፡-

- 16 ዓመት እና የጡረታ ገቢ ዕድሜ መካከል

- ዝቅተኛ ገቢ
- በሳምንት ከ16 ሰዓታት በታች በቀን በምታገኘው ገቢ መጠን ላይ ተመስርቶ የምትሰራ ከሆነ
- በሙሉ ሰዓት ትምርህት ላይ ካልሆንክ (ግን አንዳንድ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች አሉ)
- የሥራ ፈላጊዎች ወይም የሥራ ቅጥር አበል እና የድጋፍ አበል የማትቀበል ከሆነ
- ከ£16,000 በላይ የቁጠባ ሂሳቦች ከሌሉህ
- በሰሜን አየርላንድ ውስጥ ነዋሪ ከሆንክ

ወይም

- ብቸኛ ወላጅ ከሆንክ
- በአባትነት ወይም በወላጅ ፍቃድ ላይ ካለህ
- ተንከባካቢ ከሆንክ
- ከዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወደ አገር ውስጥ በስደተኝነት ደርሶ እንግሊዘኛ በመማር ላይ ያለ ስደተኛ

የሥራ ቅጥር ድጋፍ አበል (ESA)
ይህ ክፍያ ሕመም ወይም የአካል ጉዳት ስላለባቸው ለመስራት የማይችሉ ወይም በአንዳንድ የተወሰኑ ሥራዎች ላይ ለተሰማሩ ሰዎች የሚከፈል ነው። የቤት አበል በማግኘት ላይ ካለህ ፣ የሥራ ማዕከል በልዩ ሁኔታ የሰለጠነ የግል አማካሪ ይመድብልሃል። ይህም አንተን አመቺ ወደሆነ ቦታ ለማንቀሳቀስ የተቀረፁ በጣም ሰፋፊ ወሰን ያላቸው ሌሎች አገልግሎቶችን ያቀርብልሃል።

የሥራ ማዕከሉ መጠይቅ እንድትሞላ ወይም ወደ “ሥራ ብቁነት ምዘና” እንድትሄድ ሊጠይቁህ ይችላሉ። እንዲሁም ሥራ ለማግኘት የሚያስፈልጉ እርምጃዎች መውሰድ አለመወሰድህን ወይም ሕመምህ ወይም የአካል ጉዳትህ  እነዚህን እርምጃዎች ብትወስድም እንኳን ሥራህን በመፈፀም ብቃትህ ላይ ከባድ ተጽዕኖ ማሳረፋቸውን ይወስናሉ።

ይህንን ምዘና ሞልቶ ለDWP የሚልክ ዶክተር ወይም ነርስ እንዲያዩህ ሊጠሩ ይችላሉ። ሕመምህ ወይም አካል ጉዳትህ በምትሰራው ሥራ መጠን እና ዓይነት ላይ ምን ዓይነት መወሰኛ እንዳስከተሉ እና ለሥራ ቅጥር እና ድጋፍ አበል ብቁ መሆንህን ወይም ያለመሆንህን ያረጋግጣሉ።

ሁለት ዓይነት ESA አለ፡-

ከሥራ ጋር ተዛማጅ የሆነ የተግባር ቡድን - ይህ ዲደብልዩፒ ለወደፊት መስራት የምትችል መሆኑን ካመነ ነው። የሥራ ማዕከሉ በማናቸውም ሥራ ተኮር ቃለ መጠይቆች ውስጥ እንድትካፈል ይጠብቃሉ ስለዚህም ከሥራ ጋር ተዛማጅ በሆነ ተግባር ውስጥ እንድትሳተፍ ሊጋብዙህ እና ሊፈልጉም ወይም የአንተን ጥቅማጥቅም ሊቀንሱ ይችላሉ።

የድጋፍ ቡድን - ይህም ዲደብልዩፒ የአንተ ሁኔታ የምትሰራውን ሥራ ይወስናል ማለት ነው። በሥራ ተኮር ቃለ መጠይቆች ላይ እና ከሥራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ተግባራት ላይ እንደምርጫህ ለመሳተፍ ትችላለህ ።

የህፃናት ጥቅማጥቅም
ልጅህ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካሟሉ የሕፃናት ጥቅማጥቅም ለማግኘት ይቻላቸዋል፡-

- ከ16 ዓመት በታች ከሆኑ
- ከ16 ዓመት በላይ ግን ከ20 ዓመት በታች እና ለሕፃናት ጥቅማጥቅም መብት ብቁ የሚያደርግ ትምህርት ወይ ሥልጠና ላይ ካሉ።
- ከ18 ዓመታ በታች  እና ሥልጠናቸውን ወይም ትምህርታቸውን በቅርቡ ያቋረጡ - ግን ለሥራ ፣ ለትምህርት ወይም ሥልጠና ከእንክብካቤ አቅራቢዎች አገልግሎት፣ ግንኙነቶች ፣ አካባቢያዊ ባለሥልጣን ድጋፍ አገልግሎቶች ፣ የመከላከያ ሚኒስቴር ወይም ተመሳሳይ ጋር የግድ መመዝገብ አለባቸው።

የሕፃናት ጥቅማጥቅም ላይ ማናቸውንም ተጨማሪ ምክር ለማግኘት በስልክ ቁጥር 0300 200 3103  ይደውሉ

የሕፃናት ግብር ነፃ መብት
የሕፃናት ግብር ነፃ መብት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወይም የማህበራዊ ደህንነት ጥቅማጥቅም ለሚያገኙ ሰዎች የሚቀርብ ነው።

- ከ16 ዓመት በታች የሆናቸው - 16ኛ ዓመታቸውን ከያዙ በኋላ ከነሐሴ 31 ጀምሮ ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ
- ከ20 ዓመት ዕድሜ በታች - በፀደቀ ትምህርት ወይም ሥልጠና ላይ ካሉ ጥያቄውን ለማቅረብ ይችላሉ

የሕፃን ልጅ ኃላፊነት
በተለምዶ ለሕፃኑ ኃላፊነት የሚኖርብዎት ሕፃኑ፡-

- ሕፃኑ ከእርሶ ጋር በሁሉም ጊዜያት ነዋሪ ከሆነ፤
- በተለምዶ ከእርሶ ጋር እና በእርሶ ዋና ተንከባካቢነት ስር የሚኖር ከሆነ፤
- በአውሮፓ ውስጥ የሚኖር ግን በእርሶ ላይ በገንዘብ ረገድ ጥገኛ ከሆነ።

ሕፃኑ የአካል ጉዳተኛ ከሆነ
ተጨማሪ የሕፃናት ግብር ነፃ መብቶች ለማግኘት የሚችሉት፡-

- በአካል ጉዳት የተነሳ ተጨማሪ ጥቅማጥቅም ለማግኘት ይችላሉ።
- ሕፃን ልጅዎ የተመዘገበ ማየት የተሳነው (ወይም ከግብር ነፃ ይገባኛልዎ 28 ሳምንታት ውስጥ ከሆነ)

**ወደ ሥራ ማዕከሉ በሚከተሉት ሥልክ ቁጥሮች ለመደወል ይችላሉ:-**

**የስልክ ቁጥር**: 0800 055 6688 **የጽሁፍ መልዕክት**: 0800 023 4888 **እነዚህ ጥሪዎች ከመስመር ስልክ ነፃ የሆኑ ግን በተንቀሳቃሽ ስልክ ክፍያ ሊፈፀምባቸው ይችላል። የሥራ ማዕከል ቢሮው እርሶ ሊገለገሉበት የሚችሉባቸው ነፃ የስልክ መስመሮች አሉት። እንዲሁም አንዳንድ ማመልከቻዎችን በቀጥታ ለማቅረብ ይችላሉ።**

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር** : 0345 300 3900 **ወይም መስማት ለተሳናቸው ወይም የመናገር ችግር ላለባቸው በስልክ ቁጥር** 0345 300 3909 **የጡረታ ነፃ መብቶች**

**የጡረታ ነፃ መብቶች**
**ለጡረታ ነፃ መብቶ ብቁ ለመሆን፡**

- **ዩናይትድ ኪንግደም** (UK) **ውስጥ መኖር አለብዎት፤**
- **እርሶ ወይም የትዳር አጋርዎ ለጡረታ ነፃ መብት ብቁ የሚያደርግዎት ዕድሜ ላይ መገኘት አለባችሁ።**

**በጡረታ ነፃ መብት ብቁ የሚያደርግ ዕድሜ በግዛቷ የጡረታ ዕድሜ መጨመር የተነሳ ቀስ በቀስ እስከ** 66 **ዓመት ድረስ እያሻቀበ ነው።**

**የጡረታ ነፃ መብት ጥያቄ ማቅረቢያ መስመር**
**ሥልክ ቁጥር** : 0800 99 1234

**የጽሁፍ መልዕክት**: 0800 169 0133

**ከሰኞ እስከ አርብ ከ** 8am **ሰዓት እስከ** 6pm **ሰዓት**

## 4A.13 ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች

**ከታመሙ ፣ በቤተሰብዎ ውስጥ አካል ጉዳተኛ ልጅ ካለ ፣ የሆነን ሰው የሚንከባከቡ ከሆነ ወይም የሆነ ሰው እርስዎን የሚንከባከብዎ ከሆነ ወይም ለእርጅና ዕድሜ ከደረሱ።**

**የሥራ ማዕከሉን በመገናኘት በዚህ ላይ ምክር ሊሻዎት ወይም ከአካባቢያዊ የጥቅማጥቅሞች ባለሙያ ምክር ሊያገኙ ይችላሉ። የእርስዎ ሎካል ሲትዝን አድቫይዝ ቢሮ በዚህ ረገድ ድጋፍ ሊያቀርብሎትም ይችላል።** www.adviceguide.org.uk

## 4A.14 የሥራ ግብር ነፃ መብቶች

**ሥራ በመስራት ላይ የሚገኙ እና ዝቅተኛ ገቢ ያለዎት ከሆኑ ፣ የሥራ ግብር ነፃ መብቶች እንዲሁም ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ።**

**ለዚህ ጥቅማጥቅም ብዙ ለመሆን በሳምንት ለተወሰኑ ሰዓታት የግድ መስራት አለብዎት**

ዕድሜዎ ከ 25 እስከ 59 - ከሆነ በሳምንት የሰሩባቸው ሰዓታት፡ ቢያንስ 30 ሰዓታት

ዕድሜዎ ከ60 ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በሳምንት የሰሩባቸው ሰዓታት፡ ቢያንስ 16 ሰዓታት

አካል ጉዳተኛ ከሆኑ ፣ በሳምንት የሰሩባቸው ሰዓታት፡ ቢያንስ 16 ሰዓታት

ነጠላ ወላጅ ወይም 1 ወይም ከዚያ በላይ ሕፃናት ልጆች ካለዎት፣ በሳምንት የሰሩባቸው ሰዓታት፡ ቢያንስ 16 ሰዓታት

ጥንዶቹ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሕፃናት ልጆች ካሏቸው- በሳምንት የሰሩባቸው ሰዓታት፣ ቢያንስ 24 ሰዓታት (አንዳቹ ቢያንስ 16 ሰዓታት ከሰራችሁ)

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ለማመልከት በሚከተለው አድራሻ ያግኙን:-

ከግብር ነፃ የድጋፍ መስመር
ሥልክ ቁጥር : 0345 300 3900
የጽሁፍ መልዕክት: 0345 300 3909

## 4A.15 የጥቅማጥቅም ወሰኖች

የጥቅማጥቅም ወሰን በማህበራዊ ደህንነት ክፍያዎች ላይ ወሰኖችን ያስቀምጣል። አንድ ገለሰብ ወይም ቤተሰብ ሊያገኛቸው ሚችላለቸው አጠቃለይ የጥቅማጥቅም መጠኖች ቢበዛ እስከ ሚከተሉት መጠኖች ይሰጣሉ:-

- £500 በሳምንት ለነጠላ ወላጆች እና ከህፃናት ልጆች ጋር ለሚኖሩ ጥንዶች
- £350 በሳምንት ትዳር ለሌላቸው ሰዎች

ከቤት ጥቅማጥቅም ከዚህ በላይ ካሉ መጠኖች የሚዘሉ ድምር ጥቅማጥቅሞችን ለመከላከል ይቀነሳሉ።

ይህ ከፍተኛ ወሰን እርስዎ ከሥራ ውጪ ከሆኑ እና ጥቅማጥቅሞችን እንደ የገቢ ድጋፍ ፣ የስራ ቅጥር እና የድጋፍ አበል እንዲሁም የሥራ ፈላጊዎች አበል የሚጠይቁ ከሆነ ተግባራዊ ይሆናሉ። የቤት አቅርቦት ጥቅማጥቅም ሊከፈል እስከሚችለው ከፍተኛ መጠን ድረስ የሚቆጠር ሲሆን ስለዚህም ከፍተኛ የኪራይ መጠን የሚከፍሉ ሰዎች በጣም ተጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ። እርስዎ ወይም የቤተሰብ አባልዎ የተወሰኑ ጥቅማጥቅሞችን የሚያገኙ ከሆነ በዚህ ከፍተኛ ወሰን ውስጥ አይካተቱም። ይህ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ተግባራዊ አይሆኑም።

## 4A.16 በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ስለመስራት

አንድ ጊዜ የባዮሜትሪክ ካርድዎን ካገኘ የመስራት ነፃነት አለዎት። ዩናይትድ ኪንግደም (UK) የብሔራዊ ዝቅተኛ የቀን ክፍያ አላት። እባክዎን አሰሪዎ ይህንን ተመን ማክበሩን ያረጋግጡ።

ጠቃሚ ማስታወሻ:- የቀን ክፍያ አለመግባባቶች ወይም ሕገ ወጥ አሰራሮች ካሉቦት የአካባቢያዊ ዜጎች ማማከር ቢሮን ይገናኙ።

በአቅራቢያዎች ስለሚገኘው ቢሮ አስመልክቶ መረጃዎች ከ www.citizensadvice.co.uk

*ሥራ ስለመፈለግ*

*ሥራ ፈላጊ ከሆኑ ፣ የአካባቢያዊ የሥራ ማዕከል ለእርስዎ ስለቀረቡት የሥራ እድሎች ዝርዝር ለማማከር ይሂዱ። በአካባቢዎ ውስጥ የማስታወቂያ ሥራ የሚካሂዱ በጣም ብዙ ቁጥር ያላቸው የስራ አገናኝ መስሪያ ቤቶች አሉ።*

*አብዛኛዎቹ የአገር ውስጥ እና የብሔራዊ ጋዜጦች የስራ ማስታወቂያዎችን ይዘዋል። አሰሪዎ መልካም ስም እና ዝና እንዳለው እና ቢያንስ በህግ የተቀመጠውን አነስተኛ ተመን መክፈሉን ማረጋገጡ ጠቃሚ ነው።*

*ለሥራ ቅጥር ስለማመልከት*

*አሰሪዎች እንዴት ለሥራው ለማመልከት እንደፈለጉ ይደነግጋሉ።*

*በዚህ ረገድ በጣም በብዙ መንገዶች ጥያቄዎች ይቀርብልዎታል፡-*

1) *አጠቃላይ የትምህርት እና ሥራ ልምድ መግለጫ (የካሪኩለም ቪቴ) - ይህ በአብዛኛው “ሲቪ” ተብሎ ሲጠቀስ የምትሰሙት ወይም የምታዩት ነው። አሰሪው ሲቪ እንድታቀርብ ሊጠይቅህ ይችላል ይህም የሥራ ልምድ እና ሌሎች ብቃቶችህ ላይ አጠቃላይ እይታ ይሰጠዋል። የግላዊ ዝርዝሮች ፣ የትምህርት ልምድ ፣ የሥራ ቅጥር ታሪክ የበጎ ፍቃደኝነት ሥራ ዝርዝር ያስፈልግዎታል። የአከባቢያዊ የሥራ ማዕከል በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ድጋፍ ሊያቀርብልዎ ይችላል*

2) *የሥራ ማመልከቻ ቅጽ - አብዛኛዎቹ አሰሪዎች የሥራ ማመልከቻ ቅጽ እንዲሞሉ ይጠይቃሉ። ለወደፊት ቀጣሪህ ስልክ ወይም ኢሜል ማቅረብ እና የሥራ ማመልከቻ እሽግ እንዲልክልህ የመገኛ አድራሻ መስጠት አለብህ። በእዚህ እሽግ ውስጥ ስለስራህ ብዙ ዝርዝሮች ታገኛለህ። የሥራው ልዩ ልዩ መስፈርቶች ቀጣሪህ ስለሚፈልጋቸው ብቃቶች ወይም ልምዶች ይናገራሉ። ያሉህን ብቃቶች እና ልምዶች ከምታመልክትበት የሥራ መደብ ልዩ ልዩ መስፈርቶች ጋር ማዛመዱ በጣም አስፈላጊ ነው።*

3) *ቃለ መጠይቅ - አሰሪህ አንድ ጊዜ ማመልከቻህን ከተመለከተ በኋላ ፣ ለተጨማሪ የሥራ ምቹነት ማረጋገጫ ምዘና ለማድረግ ቃለ መጠይቅ ትካፈላለህ። ይህም ከአንድ ግለሰብ ወይም የቅጥር ቡድን ጋር ሊሆን ይችላል። ከሥራ ማመልከቻ ቅጽህ፣ ከሥራ ልምድህ፣ ከክህሎቶችህ እና ሥራውን ለምን እንደፈለግከው ጥያቄዎችን ሊያቀርቡልህ ይችላሉ። ልትሰራበት ስላቀድከው ኩባንያ ከቃለ መጠይቁ በፊት ምርመራ ማካሄድ እና እንድትሰራው ስለተጠየቅከው ሚና ሙሉ መረዳት ቢኖርህ ጥሩ ሀሳብ ነው። ልትጠየቃቸው ስለምትችላቸው ጥያቄዎች እና እንዴት ልትመልሳቸው እንደምትችል በሚገባ አስብ።*

*ስኬታማ በሆነ መልኩ ሥራ አገኘህን?*

*የወደፊት አሰሪ ድርጅት ሥራ ከመጀመርህ በፊት ለሥራው ስላለህ ብቁነት ለማረጋገጫ ዓላማ የሚውሉ ጥያቄዎች ይጠይቅሃል። ይህንን ለማረጋገጥ የአንተን ባዮሜትሪክ ካርድ ማሳየት ያስፈልግሃል። እንዲሁም ሥራ ለመጀመር ባያስፈልግህም እንኳን የብሔራዊ መድህን ቁጥረ ማቅረብም ያስፈልግሃል። የቀን ክፍያዎችህ ወዲያውኑ ግብር እና የብሔራዊ መድን ተቀናሽ ሊደርግላቸው ይገባል። ከአንድ በላይ የሆኑ ሥራዎች ካሉህ ፣ ለአሰሪህ እና ለግብር ቢሮ*

በማስታወቅ ግብርህን አሳንሰህ እንደማትከፍል ለማረጋገጥ የግብር ኮድ ሊለውጡልህ ይችላሉ።

የራስ ተቀጣሪ/አነስተኛ የንግድ ሥራ
የራስ ተቀጣሪ ወይም የራስህ የንግድ ድርጅት ባለቤት ለመሆን ትመኛለህ። ብዙ ሰዎች ይህንን በተሳካ መልኩ አድርገውታል። የብደር ወይም የልገሳ ማመልከቻ ልታቀርብ ትችላለህ። እንዲሁም በዚህ ረገድ ምን ዓይነት ድጋፍ ለማግኘት እንደምትችል ለማረጋገጥ ከአካባቢያዊ የዜጎች ምክር አገልግሎት ምክር ማግኘት ትችላለህ። የግብር እና የብሔራዊ መድህንን አስመልክቶ የግብር ቢሮን ማነጋገርም ያስፈልግሃል።

ለዝውውር ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች
በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ሊታወቁ የማይችሉ ብቃቶች ካለህ ፣ የሚከተለው ድርጅት ድጋፍ ሊያቀርብልህ ይችላል፡-

NARIC ነፃ ምክር፡-

ስደተኛ ከሆንክ በስልክ ቁጥር 0870 990 4088 ስለብቃቶችህ ነፃ ምክር ለማግኘት ትችላለህ

## 4A.17 የብሪታኒያ ዜግነት የማግኘት መብት

ለዚህ መብት ከማመልከትህ በፊት ሰባት መስፈርቶችን ማሟላት ያስፈልግሃል፡-

- ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ መሆን
- በጣም ጤነኛ አእምሮ (ስለ ድርጊቶችህ ሙሉ መረዳት ያለህ)
- በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ መኖር የዘውድ አገልግሎት፣ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) አባል በሆነችበት አለም አቀፍ ድርጅት አገልግሎት ወይም በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ለተቋቋመ ኩባንያ ወይም ማህበር አገልግሎት ለማቅረብ መቀጠል የምታስብ
- ተቀባይነት እስካለው ደረጃ ድረስ በእንግሊዝኛ ፣ በዌልስኛ ወይም በስኮትላንድ ጋሌክ ቋንቋ የመግባባት ችሎታ
- በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ስላለው ሕይወት በቂ እውቀት ሊኖርህ ይገባል
- ጥሩ ፀባይ መገለጫህ የሆነ ስብዕና
- የነዋሪነት መስፈርቶችን (ከዚህ በታች ተመልከቱ) ማሟላት አለብህ።

ለብሪታኒያ ዜግነት የስደተኛ ጊዜ ገደቦች።
ለዩናይትድ ኪንግደም (UK) ዜግነት የስደተኛ ጊዜ መወሰኛዎች (አንድ የውጪ አገር ዜጋ ዜግነት የሚያገኝበት ሂደት) ነፃ መሆን አለብህ። ባለፉት 12 ወራት የነዋሪነት ብቁነት ጊዜያት ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) ዜግነት የስደተኛ ጊዜ መወሰኛዎች ነፃ መሆን ይገባሃል።
ይህም ማለት ያልተወሰነ የፍቃድ ቆይታ ከተሰጠህ 12 ወራት በኋላ ማመልከት ትችላለህ።

በእነዚህ የነዋሪነት ማብቂያ ቆይታ ጊዜያት በመላ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ በሕጋዊነት ስትኖር መቆየት አለብህ። በተባለው ጊዜ ውስጥ የስደተኝነት ሕጎችን ጥሰህ ከተገኘህ ዜግነት ከማግኘት ውድቅ ልተደረግ ትችላለህ። ምን ዓይነት መወሰኛዎች ጥሰቱን እንዳስከተሉ

ተመስርቶ በዚህ የነዋሪነት መስፈርት ላይ አንዳንድ ግለ ውሳኔ ሊንቀሳቀስ ይችላል።

ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) አገር ውጪ የነበረህ ቆይታ ጊዜያት
ማመልከቻውን ከማቅረብህ በፊት ከዩናይትድ ኪንግደም (UK) አገር ውጪ ከ450 ቀናት በላይ መቆየት አይኖርብህም።

ማመልከቻውን ከማቅረብህ በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ ከእንግኪዝ አገር ውጪ ከ90 ቀናት በላይ ቆይታ ማድረግ አይኖርብህም።

እነዚህን የነዋሪነት መስፈርቶች ካላሟልህ ግን በአንተ ጉዳይ ውስጥ ልዩ ሁኔታዎች እንዳሉ ካመንክ ፣ ማመልከቻን ስታቀርብ ማብራሪያ ማድረግ ይኖርብሃል።

ጥሩ ፀባይ
ጥሩ ፀባይ መገለጫህ እንዲሆን የዩናይትድ ኪንግደም (UK)ን ሕጎች እና ግዴታዎች መከተል ይኖርብሃል።

ማናቸውም የወንጀል ጥፋቶች ካሉብህ ጥሩ ፀባይ እንዳለህ ተደርጎ አይቆጠርም።  እነዚህም የሚያካትቷቸው  የወህኒ ቤት እስር ፣ የወንጀል ቅጣት ወይም የማህበረሰብ አገልግሎት ይሆናሉ። እነዚህ ነገሮች እስኪፋቁ ድረስ ዜግነት ልታገኝ ፈጽሞ አይቻልህም። ይህ መዝገቡ ከመፋቁ በፊት እስርህን ካጠናቀቅክ በኋላ የሚኖርህ ጊዜ ነው።  ይህም ከ 3 እስከ 15 ዓመታት ይደርሳል። Home Office እስከ 4 ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ ለታሰረ ግለሰብ ዜግነት ሊሰጥ አይችልም።

ለሕፃናት ልጆች የብሪታኒያ ዜግነትን ስለመስጠት
በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ እንድትቆይ “ያልተወሰነ ጊዜ ቆይታ” ተሰጥቶህ ከነበረ ፣ እና ከዚህ በፊት በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ የተወለደ ልጅ ካለህ ፣ ሕፃን ልጅህን በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ዜግነት ማስመዝገብ ትችላለህ።

“ያልተወሰነ ጊዜ ቆይታ” ፍቃድ ተሰጥቶህ እያለ ልጅ ከወለድክ በመቀጠል ሕፃን ልጅህ በትውልድ እንግሊዛዊ ይሆናል። ተጨማሪ እርዳታ ካስፈላጋችሁ ወደ www.gov.uk/becoming-a-british-citizen/check-if-you-can-apply አስተውሉ ይህ የዜግነት ማመልከቻ ለማቅረብ የተለያዩ የሚከፍል ሒሳብ አለ።

## 4A.18 የቤተሰብ ዳግም ቅልቅል

የሰብአዊ አድራጎት ጥበቃ ወይም የስደተኛ ሁኔታ ተሰጥቶህ ከሆነ ፣ ለቤተሰብ ዳግም ቅልቅል የመልከት መብት አለህ። የቤተሰብ ዳግም ቅልቅል መብት በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ነባር - ቅድመ የቤተሰብ አባልን የመቀላቀል መብት። እነርሱም በፍቃድህ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ስር አንተን ለመቀላቀል ይቻላቸዋል።

ይህም ሊያካትታቸው የሚቻላቸው :- ሚስት/ባል ፣ የሕግ የትዳር ጓደኛ እና ጋብቻ ያልፈፀሙ /የተመሳሳይ ፆታ የትዳር አጋሮችን ነው። እንዲሁም ይህ በአንተ እና አንተ በስደት ላይ እያለህ የቤተሰብህን ክፍል በሚመሰርቱት ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናትን ነው። በተጨማሪ አንተ

ወደውጪ አገር ከመሄድህ በፊት ተጸንሰው የነበሩ ሕፃናት ልጆችን ያካትታል።

Home Office የስደተኛ ደንቦች ውጪ ጉዳያቸው በአሳዛኝ ምክንያቶች የተነሳ ሊታዩላቸው ለሚገቡ ሌሎች የቤተሰብ አባላትህ የቤተሰብ ዳግም ቅልቅልን ሊፈቅድ ይችላል። ተጨማሪ መረጃ ስለዚህ ጉዳይ የሚመለከት ካስፈለጋችሁ በ Home Office (ሆም ኦፊስ) ዌብ አድራ ይመለከቱ።
www.gov.uk/settlement-refugee-or-humanitarian-protection/family-reunion

## 4A.19 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎች

እንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃትህን ለማሻሻል ትችላለህ። ይህ በዩናይትድ ኪንግደም (UK) ውስጥ ካለው የአኗኗር ዘይቤ ጋር በይበልጥ ለመላመድ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ለመጠናከር ታላቅ ጠቀሜታ አለው። ትምህርትን ለመከታተል ፣ በቀን ተቀን አኗኗር ሕይወት ውስጥ ድጋፍ ለማግኘት እና ለመላመድ እንዲያግዝህ እንዲሁም ሥራ ለማግኘት እንዲረዳህ እንግሊዝኛ ቋንቋን መማር ታላቅ ጠቀሜታ አለው። የ ESOL ትምህርት ክፍሎች (እንግሊዝኛ ሌሎች ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ሰዎች) ላይ መማር ትችላለህ። በዚህ ረገድ በሚመጥንህ የቋንቋ ደረጃ ትምህርቱን ለመጀመር ትችላለህ። አስቀድሞ የነበረ እንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ደረጃ አስመልክቶ በሚቀርብ ምዘና ምቹ ምደባ ይደረግልሃል። የምትማራቸው ትምህርቶች

- የእንግሊዝኛ ቋንቋን መናገር
- የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማዳመጥ
- የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማንበብ እና መፃፍ
- መዝገበ ቃላት
- ሥርዓተ ነጥብ እና ሰዋሰው

ለESOL ትምህርት ለማመልከት በአካባቢው የሚገኘውን ተጨማሪ የትምህርት ኮሌጅ መገናኘት ትችላለህ።

ኮርሶቹ በአጠቃላይ መስከረም ወር ላይ ይጀምራሉ። ምቹ የESOL ኮርስ የሚያቀርብ ኮሌጅ የማግኘት ችግር ከገጠመህ ፣ የአካባቢውን የስራ ማዕከል በዚህ ረገድ ድጋፍ መሻት ትችላለህ።

ክፍያ መክፈል ይኖርብኛልን?

እንግሊዝ
ESA ላይ ተመሰረርቶ የሥራ ቅጥር ያገኙ ወይም የሥራ ፈላጊዎች አበል የሚወስዱ ከሆነ ፣ ነፃ እንግሊዝኛ ትምህረት ክፍሎችን የማግኘት እድል ይኖርዎታል።

Wales (ዌልስ)

በ Wales (ዌልስ) የእንግሊዘኛ ትምህርት ESOL (ኢ.ሶ.ዖ.ል) የሚባል ትምህርት ያለክፍያ ይሰጣል።

ስኮትላንድ
ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍሎች በሚከተሉት አማካኝነት ድጋፍ መሻት ይችላሉ፡-

- በከፍተኛ ትምህርት (HE) ውስጥ ክፍያ እና የተማሪ ድጋፍ
- በተጨማሪ ትምህርት (FE) ውስጥ ነፃ የክፍያ መብት እና እንደየሁኔታው የሚወሰን ድጋፍ

በኮርሱ መጀመሪያ ቀን ላይ እንደ ማንኛውም ተራ ነዋሪ ይህንን ማድረግ ትችላለህ።

ሚስት፣ የሕጋዊ ትዳር አጋር ወይም ሕፃን ልጅ በስኮትላንድ አገር የመደበኛ የነዋሪነት መስፈርትን ካሟሉ ብቁ ለመሆን ይችላሉ። ለግለሰባዊ የመማሪያ ሂሳብ ወይም ለትምህርት መኖሪያ አበልም ብቁ ለመሆን ትችላለህ።